# ፌደሬሻችንን ለመከፋፈ ሁለተኛ ዘመቻ

ሲራክ ከሚድዌስት

አላሙዲን ፌዴሬሹን ለመቆጣጠር ያደረገውን ከፍተኛ የገንዘብ ብተና ዛሬ ታሪክ ሆኖ የምናስታውሰው ጉድ ነው፡፡ ጥቂት ሆዳሞች ለሆቴልና ለበረራ ከተከፈለ ምን አገባን በማለት እፍራሽ በመሆን የተሰለፉትን ሰዎች በየአካባቢያችን እናውቃቸዋለን፡፡ ምስጋና ለኢትዮጵያውያን ይሁንና የአላሙዲን ሴራ እንዳይሆን ሆኖ ተንኮታኩቷል፤፤

ይህን የምንወደውን ፌዴሬሽን ለመከፋፈል ዛሬ ደግሞ እፍቃሪ አላሙዲ የሆነው ብዙ የሚያወራውና ብዙ ሽርሽር የሚወደው ጠቅላይ ሚኒስቴር የስፓርት ፌዴሬሺኑን ለመከፈል ወይም የወያኔ ለማድረግ የወሰነ ስለመሆኑ ሚስጢር እይደለም፤፤ ጋብዙኝ እመጣለሁ ማለቱ በሰፊው እየተወራ ነው፡፡

ይህ_ፌዴሬሽን_ሁለት_አማራጭ_አለው፡-

**እንድ** እጅ ነስቶና ተንበርክኮ የጠ/ሚ ጥያቄ እስተናግዶ ወደ ስታዲሞ በመጋበዝ ሰፊውን የዲያስፓራ ኢትዮጵያውያንን መከዳት ሲሆን

**ሁለተኛው** አማራጭ ደግሞ ከበርካታው ኢትዮጵያውያን ጋር ወግኖ ፌዴሬሹን ማዳን ነው፡፡ የጠ/ሚኒስትሩን ጥያቄ ውድቅ ማድረግ ነው፡፡ የሚመረጠውም ይሄ ነው፡፡

**ህጋዊ_ማስታወሻ**

ይህ ፌዴሬሺን በአሜሪካ መንግስት ህግ መሰረት የተመዘገበው አትራፊ ያልሆነ ድርጅት( nonprofit) በመሆን ሲሆን ከማንኛውም የፓለቲካ ወይም የሃይማት ጋር የማይወን ነው፡፡ የወያኔን ፓለቲካ ማራመድ ከቆመለት አላማ ጋር የሚቃረን በመሆኑ በህግ ላለመጠየቅና ሰፊውን የዲያስፓራውን ኢትዮጵያ ላለማስቀየም መወሰን አለበት፤፤

ይህን ወያኔ ካስተናገዳችሁ ግን ላለፈው በርካታ አመታት የዘለቀው ፌዴሬሽን እድሜው ማጠሩን መጠራጠር የለባችሁም፤፤

ህዝባዊው ፌዴሬሺናችን ህልውናውን ይዞ የወያኔንም ከፋፋይ ሴራ መክቶ በድል ይወጣል የሚል እምነት አለኝ፡፡

እንበርታ!!!